የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፲፮
አዲስ አበባ የካቲት ፲፪ ቀን ፲፱፻፺፱

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

13th Year No 16.
ADDIS ABABA 19th February, 2007

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፭፻፲፮/፲፱፻፺፱ ዓ.ም

የኢትዮ-ጂቡቲ ልዩ የኢንቨስትመንት ማመቻቻ እና የንብረት ባለቤትነት ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር … ገጽ ፫ሺ፭፻፸፭

CONTENTS

Proclamation No. 516/2007

The Ethio-Djibouti Preferential Investment Facilitation and Property Acquisition Agreement Ratification Proclamation Page 3575

## አዋጅ ቁጥር ፭፻፲፮/፲፱፻፺፱

### የኢትዮ-ጂቡቲ ልዩ የኢንቨስትመንት ማመቻቻ እና የንብረት ባለቤትነት ስምምነትን ለማጽድቅ የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በጂቡቲ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የተደረገው ልዩ የኢንቨስትመንት ማመቻቻ እና የንብረት ባለቤትነት ስምምነት ኅዳር ፱ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም ጂቡቲ ላይ የተፈረመ ስለሆነ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥር ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ /፩/ እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የኢትዮ-ጂቡቲ ልዩ የኢንቨስትመንት ማመቻቻ እና የንብረት ባለቤትነት ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፭፻፲፮/፲፱፻፺፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION NO. 516/2007.

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE ETHIO-DJIBOTI PREFERENTIAL INVESTMENT FACILITATION AND PROPERTY ACQUISITION AGREEMENT

**WHEREAS,** the Agreement, on Preferential Investment Facilitation and Property Acquisition between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of Republic of Djibouti was signed at Djibouti on the 18th day of November 2006.

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Agreement at its session held on the 6th day of February, 2007.

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 Sub-Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. **Short Title**

This Proclamation may be cited as "The Ethio-Djibouti Preferential Investment Facilitation and Property Acquisition Agreement Ratification Proclamation No. 516/2007."

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

## ፪. ስምምነቱ ስለመጽደቁ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በጂቡቲ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል ኅዳር ፱ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም ጂቡቲ ላይ የተፈረመው ልዩ የኢንቨስትመንት ማመቻቻ እና የንብረት ባለቤትነት ስምምነት ፀድቋል።

## ፫. የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሥልጣን

ይህ ስምምነት በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥልጣን ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በዚህ አዋጅ ተሰጥቷል።

## ፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ የካቲት ፲፪ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

## 2. Ratification of the Agreement

The Ethio-Djibouti Preferential Investment Facilitation and Property Acquisition Agreement signed at Djibouti on the 18th day of November 2006 is hereby ratified.

## 3. Power of the Minister of Trade and Industry

The Minister of Trade and Industry is hereby empowered to implement this Agreement.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall come in to force up on Publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 19th day of February, 2007**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት